# አታካቹ ተቃዋሚ

**ድንቁ ጣሰው 12-10-14**

ከርሞ ጥጃ ይላል የሀገራችን ሰው አድሮ ቃሪያም በሚል ይገልፀዋል፡፡ እዚያው…እዚያው የሚለውን፣ የማይለወጠውን፣ ተለውጦም የማይታየውን፣ መለወጥን ማደግን የማያውቀውን፣ የሚገልፅበት መንገድ መሆኑ ነው፡፡ ጭቃ ውስጥ ተዘፍቆ ገብቶ እዚያው …እዚያው እየተሽከረከረ እየተንፈራፈረ ከገባበት መውጣት ያልቻለ ጎማም እንዲሁ ነው፡፡ እነዚህ አገላለፆች በትክክል የእኛን ተቃዋሚ ፓርቲዎች የሀገር ውስጡንም የውጪውንም ይወክላሉ፡፡

ከዛሬ አርባ ዓመት፣ ከሃያ ዓመትም፣ ከአሥር ዓመት በፊትም፤ ትናንትም ዛሬም እዚያው ላይ ናቸው፡፡ የአስተሳሰብና የአመለካከት ለውጥ የላቸውም፡፡ እወቅ ያለው በልጅነቱ እንዲሉ አንድ ሰው ተወልዶ አርባ ዓመት ከሞላው ብዙ የሕይወት ተሞክሮዎችን ያሳለፈ፣ ጉርምስናንም የተሻገረ ጎልማሣ ሆኗል ማለት ነው፤ ሌላው ቀርቶ በእድሜ እንኳን ሲለካ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፖለቲከኞች በዚህ አልበቃቸውም፡፡

ሕሊናቸው፣ አስተሳሰባቸውና ፖለቲካዊ እይታቸው መስፋትና በርቀት መመልከት ማመዛዘን የማይችል ትልቅ በሆነ የአመለካከትና የአስተሳሰብ ድህነት የተጠቃ ተቃዋሚ ነው ያለው፡፡

በጥላቻና በእልህ የተዋጠ፣ የሰለጠነ የፖለቲካ ባህል የሌለው፣ በስድብና በነውረኛነት የተሰሩትን ለሀገር የሚበጁ ታላላቅ ሥራዎች ሁሉ በማጥላላትና ጥላሸት በመቀባት የግለሰቦችን ስብዕና በሀሜትና በአሉባልታ የሚያብጠለጥል፣ ሁሌም ለበጎ ሳይሆን ለእኩይ ሴራ ተሰልፎ የሚውልና የሚያድር፣ የተሻለ አማራጭ የሌለው ተቃዋሚ ፖለቲከኛ የትም ሀገር ላይ የለም፡፡

የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች በሀገር ውስጥም በዳያስፖራም ላሉት ተቃዋሚ መሆን ማለት ህግና ሥርዓትን መርገጥ፣ ሥነ ምግባር በጎደለው መልኩ

በፈጠራ ወሬ ስም ማጥፋት፣ በቅጥረኛ የግል ጋዜጦቻቸው አማካይነት ተራ የመንደር ወሬና አሉባልታን ማናፈስ፣ ጥላቻን መዝራት፣ የእነሱን አካሄድና አስተሳሰብ ለሚቃወሙ ወይንም በማይከተሉ ሰዎች ላይ ይህ ቀረሽ የማይባል የስብዕና ማብጠልጠል ማካሄድ ነው፡፡

ሀሳብን በሀሳብ የሚሞግቱ፣ የሚከራከሩ፣ የተሻለ ሀሳብና አመለካከት በአሸናፊነት እንዲወጣ የጋራ መስመር ሆኖ እንዲቀጥል ማድረግ ሳይሆን ለተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲነት የማይመጥን አካሄድ ይዘው ሀገርን እንመራለን ብለው ማሰባቸው ለሕዝብ ንቀትና ስድብ ነው፡፡ ወሣኝ የሆነውን ሕዝብ አሳንሶና አዋርዶ የመገመት ያህል ነው፡፡

የፖለቲካ አሠራራቸውና አካሄዳቸው ለሀገርና ለህዝብ በሚበጅ መልኩ የተሰላና የታለመ ሳይሆን ቡድናዊ የሥልጣን የበላይነትን ለማግኘት ሲሉ ብቻ የሚያካሂዱት ሩጫ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለሀገርም ለሕዝብም አንድም ምንም ፋይዳ የለውም፡፡

ምርጫ ደረሰ ወይም መጣ ሲባል ከያለበት ከምርጫ ቦርድ ያወጡትን አቧራ ሲጠጣ የከረመ ወይንም የተረሳ ፋይል ውስጥ የተቀመጠ የምዝገባ ፈቃዳቸውን አራግፈው ይዘው በመውጣት ምርጫ ቦርድ ሄደው በመመዝገብ ለመወዳደር ዝግጁ ነን ብለው መለያና መታወቂያ ዓርማም ይሰጠን የሚሉ ስመ ብዙ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ያሉባት ጉደኛ ሀገር ናት ኢትዮጵያ፡፡

አለን ቢሉም ኖረው የማያውቁና የሌሉ ስማቸው ብቻ ያለ፤ መሪ ነን የሚሉትም ዘመድ አዝማዶቻቸውን ወይንም አብሮ አደግ ጓደኞቻቸውን አሰባስበው ሀምሳ እና አርባ ሰው ይዘው ተቃዋሚ ፓርቲ ነን ብለው ሲያወሩ ጥቂት ይሉኝታ ሀፍረት የሚባል ነገር ያልፈጠረባቸው ሰዎች ያሉባት ሀገር ነች ኢትዮጵያ፡፡ ይኼ በሀገርና በሕዝብ መቀለድ ብቻ ሳይሆን ማሾፍም ጭምር ነው፡፡

በአንድ ወቅት በፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ውድድር ወቅት በተደረገ የፊት ለፊት ውይይት ተቃዋሚ ፓርቲ መሪ ነኝ የሚሉት ግለሰብ እስቲ የፓርቲዎትን ፕሮግራም ይግለፁ ተብሎ ሲጠየቁ ፕሮግራም ምን ያስፈልጋል? እሱን በምርጫ ካሸነፍን በኋላ አብረን እንሰራዋለን ሲሉ በቴሌቪዥን መስኮት ይከታተል የነበረው በሚሊዮኖች የሚቆጠር ሕዝብ በያለበት ተንከትክቶ ተንፈርፍሮ እንደሳቀ ሁሉም ያውቃል፡፡

ግማሹ በጎጥ ፖለቲካ ፓርቲነት በየክልሉ የተደራጀ ሆኖ በቅጡ የተቀረፀ ሕገ ደንብም ሆነ የፓርቲ መተዳደሪያ የአባላት ሥነ ምግባር ደንብ ወዘተ…የለውም፡፡ በብሔራዊ ደረጃ ስሙን ይዘው የኢትዮጵያ ምናምን ፓርቲ…ምንትርሴ ፓርቲ የሚሉትም ከሁለትና ሦስት ከሚባሉት ውጭ ማንነታቸውም ተረስተው ኖረው ደግሞ እነዚህ እነማን ናቸው? እስኪባሉ ድረስ ይህንኑ የፈረደበትን የምርጫ ጊዜ ጠብቀው ብቅ የሚሉ ወይም የሚግተለተሉ ናቸው፡፡

የተቃዋሚው አመራር አብዛኛው በተለያዩ ሙያ ላይ የመንግሥት ሠራተኛ የነበሩ፣ በእድሜ የገፉ፣ በጡረታ ላይ የሚገኙ ሰዎች ለጊዜ ማሳለፊያ ወይንም ለተጨማሪ ገቢ ማግኛ ለስም ብቻ ተቋቁመው ስም ይዘው ያሉ ናቸው፡፡

እንደነዚህ ዓይነት ሰዎችና እያንጎላጁ ያሉ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በሀገር ግንባታ ለመሳተፍ፣ አዲሰ ሀሳብ ለማፍለቅ፣ የአመለካከት ለውጥ ለማድረግ ፈቃደኝነቱ የላቸውም፡፡

የዓለምን ሆነ የአካባቢውን እንዲሁም የሀገሪቱን ተጨባጭ ፖለቲካና እውነት ለመረዳት ፍፁም ችግር አለባቸው፤ አማራጭ ሆነው የተሻለ መንገድ ፖሊሲ አቅጣጫ ማሳየትም ሆነ ማፍለቅ አይሹም፡፡ ችክ ያለ ጥላቻና የአመለካከት ድርቀት ውስጥ የሚገኙ የተሻለ እንስራ ቢሉ እንኳን ሰርተው ለማሳየት የማይችሉ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ሀገሪቱ አሁን ያለችበትን እድገትና ለውጥ ማስቀጠል የማይችሉ ጎታች ኃይሎች ናቸው፡

ተቃዋሚ ነን የሚል ስም ይዘው ትንሽ ሸቅጠውም ሆነ ነግደው ያገኟትን ይዘው ምርጫው ሲያበቃ የት እንደሚደርሱ የት እንዳሉ እንኳን አይታወቅም፡፡ ደሞ ሌላ ምርጫ እስኪመጣ እድሜ ካገኙ ይመጣሉ፡፡ ኢንጂነር ይልቃል ሰብስቧቸው ዘጠኝ የተባሉት ተቃዋሚ ፓርቲዎች እነዚሁ ናቸው፡፡

ታዲያ ይኼ ለኢትዮጵያ ህዝብ ትልቅ ስድብና ንቀትም ነው፡፡ ትልቅ ስም አለን የሚሉትም በራሳቸው ጊዜ በራሳቸው ባህርይና ማንነት በእብሪትና በእኔ ነኝ የበላይ ሙት ፖለቲካቸው ተዘፍቀውና ተነክረው እየተበላሉ ይኖራሉ፡፡ እንኳን ለህዝብ የሚበጅ ሥራ ሊከውኑ ለራሳቸውም መሆን አልቻሉም፡፡

የማይተማመን ባልንጀራ በየወንዙ ይማማላል እንዲሉ አንዴ ገጥመው ሲያውካኩ ፍቅራቸው ክንፍ ሲል በሌላ ጊዜ ደግሞ ተጣልተው ተኮራርፈው በጠላትነት ሲተያዩ ሲፈላለጉ አንዱ ሌላውን ሊያጠፉ ሲያደባ ስም ሲያጠፉ ኧረ የት አባቱ ደሞ እሱ ብለው ...ሲባባሉ የሚገኙ ስማቸው ትልቅ ሥነ ምግባራቸውና አስተሳሰባቸው እጅግ በጣም ትንሽና የወረደ የዘቀጠ የሆኑ ብዙዎች አሉ፡፡

ዛሬም ይህንኑ ባህሪያቸውንና ዘመን የማያርመውን እኩይ አስተሳሰብና ድርጊታቸውን እያየን እየመሰከርን ነው፡፡ አንድና ተመሳሳይ ዓላማ ይዘው ተለያይተው የተለያየ ፓርቲ እየፈጠሩ እርስ በእርስ ሲዶላለቱ ሲወነጃጀሉ ነግቶ ይመሻል፡፡ እነዚህን አምኖ የሀገር አደራ የሚሰጥ የሚመርጣቸው ሕዝብ የለም፡፡ ሀገርም ህዝብም መጫወቻ አይደሉምና!

ነገ በዚህ የቆሸሸ ሥነ ምግባራቸውና አስተሳሰባቸው ሲባሉ ወንበሩ ለእኔ ይገባል ለእኔ ሲባባሉ ሲገዳደሉ ሀገሪቷንም ሕዝቡንም ለከፋ አደጋ አሳልፈው እንደሚሰጡት ለሰከንድ አያጠያይቅም፡፡

በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ የተቃዋሚ ፓርቲ መመሥረት መንግሥትን አክርሮ መቃወም፤ የግሉ ፕሬስ የመፅሔትና የጋዜጣ ባለቤትና ጋዜጠኛ መሆን እጅግ በሚያስገርምና በሚደንቅ ሁኔታ ትልቅና ምንጩ የማይገለጽ የሸፉን ገቢ የሚያስገኝ የብዙ ግለሰቦችን ሕይወት ሙሉ በሙሉ የለወጠ ንግድ ነው፤ ቢዝነስ ነው፡፡በሀገርና በህዝብ ስም እየተነገደ ግለሰቦች የሚከብሩበት መስክ ነው፡፡

በመቃወማቸው ከባህር ማዶ የሚጎርፍላቸው ገንዘብ ለተቃዋሚ ፓርቲዎችና ሆነ ለግል ፕሬስ ባለቤቶች በቀላሉ የማይቆጠርና ግብር የማይከፈልበት፣ ታክስ የማይጠየቅበት ነው፡፡

ያለማፈር በዴሞክራሲ፣ በሰብዓዊ መብት፣ በፕሬስ ነፃነት ስም የፖለቲካ ምህዳሩ ጠቧል በሚል መነገጃ  የዋሁና ቅኑ ሕዝብ እውነት እየመሰለው ለሀገርና ለወገን የቆሙ ተቆርቋሪዎች ጀግኖች የሕዝብ ልጆች እያለ ያወድሳቸዋል፡፡ በእሱው ስም እንደሚነግዱበት እንደሚያተርፉበት እነሱ የተጫጫሰ ዘመናዊ ንግድ ውስጥ መሆናቸውን ሙሉ በሙሉ አያውቅም፡፡

ተቃዋሚ ፓርቲዎችም ወደውጭ ሀገር ለመሄድ ወደአውሮፓ ለመሻገር የፈለገ ሰው በደላላ እያፈላለጉ ከፍተኛ ገንዘብ እያስከፈሉ የእከሌ ተቃዋሚ ፓርቲ አባል ነው፤ መንግሥት ከፍተኛ ጫናና ክትትል ስለሚያደርግበት(ባት) ለሕይወታቸው አስጊ ስለሆነ ከሀገር ለቀዋል ትብብር ይደረግላቸው እየተባለ ፓርቲው ውስጥ አባል መሆን ቀርቶ ፓርቲ ምን እንደሆነ እንኳን የማያውቁ ሰዎች ስንቱና ስንቱ ባህር ማዶ ተሻግሯል፡፡

ገንዘቡም የተቃዋሚ ፖለቲካ መሪዎቹ የግል መጠቀሚያና ቢዝነሳቸው ስለሆነ ማንም የሚጠይቃቸው የለም፤ ተቃዋሚው የሚልከው ወደ አሜሪካና አውሮፓ ሲሆን ዐረብ ሀገር ሰዎችን የሚልኩ ኤጀንሲዎችና ደላሎች እንደሚሰሩት እነዚህም የተቃዋሚ ፓርቲ መሪ ነን የሚሉት የፖለቲካ ደላሎች በሀገርና በሕዝብ ስም እየማሉና እየተገዘቱ ነው እንዲህ ዓይነቱን ሥራ የሚከውኑት፡፡

ዛሬ በደቡብ አፍሪካ ውስጥ ከአስራ ሰባት ዓመታት በላይ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት ናቸው እየተባሉ ከያኔዎቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በሚያገኙት ማረጋገጫ ወረቀት ሁለት አውራጃ ለመሙላት ምንም ያህል ያልቀራቸውን እዚያው ተዋልደው የተባዙትን ደቡብ አፍሪካ በስደት የሚገኙትን ዜጎቻችንን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ሀገርህ ላይ ሆነህ ጠንክረህ ሥራ፣ ተለወጥ፣ ሀገርህን ገንባ አይደለም ተቃዋሚው የሚለው፤ ስደትን የሚያበረታታ ነው፡፡

ይቅር ተቃዋሚ ሊሆኑ ቀርቶ ፓርቲ የሚባል ነገር ሰምተውም የማያውቁ ስንቶች በተቃዋሚ ፓርቲ አባልነት ስም ስደት ወጥተዋል፤ እውነቱ የኢኮኖሚ ስደተኞች እንጂ የፖለቲካ ስደተኞች አይደሉም፡፡ በዚህ ዓይነቱ የውንብድናና የወንጀል ንግድ የከበሩ እቁባቶቻቸውን የቤተሰብ አባልና ዘመዳ ዘመዳቸውን ባህር ማዶ ያሻገሩ አገር ቤት ያሉትም ውጭ የወጡትም ሕሊናቸው ያውቀዋል፡፡ ሽፋኑም መንግሥት ስለሚከታተላቸውና በሀገር ውስጥ መኖር ስለማይችሉ የውጭ መንግሥታት የስደተኛ ድርጅቶች፣ የሰብዓዊ መብት ተቋማት ትብብር ያደርጉላቸው ዘንድ እንጠይቃለን በሚል መሆኑ ይታወቃል፡፡

የእከሌ ተቃዋሚ ፓርቲ እየተባለ 23 ዓመታት ሲነገድ፣ ሲሸቀጥ፣ ንግድ ሲሰራ ኖረ፡ ፡ ይህንን ተከታትሎ የደረሰበት የአዲስ አበባ ማፍያም የራሱን ፎርጂድ ሥራ

ሲከውን ኖረ፡፡ መንግሥትንና ገዢውን ፓርቲ መቃወም ከፍተኛ ገንዘብ የሚያስገኝ የጦፈ ቢዝነስ ሆኖ ቀጥሏል፡፡

በአንድ ወቅት ከተለያዩ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ይህንን ወረቀት እየገዙ ወይንም ጥገኝነት እንዲያገኙ በከፍተኛ ግዢ እየተላከላቸው ባህር ማዶ የገቡ ኢትዮጵያውያን ጉዳይ ያሳሰባቸው መንግሥታት አንድ መላ ዘየዱ፡፡

የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች ሙሉ ስማቸውን፣ የፓርቲዎቹን አርማ፣ መተዳደሪያ ደንቡን፣ የመሪዎቹን ስም በሙሉ ሰብስበው ከአማርኛ ወደ እንግሊዘኛ አስተርጉመው ይኸው የስደተኞችና የጥገኝነት ጠያቂዎች ጉዳይ በሚታይባቸው ፍርድ ቤቶች በቋሚነት እንዲቀመጡ አደረጉ፡፡

ባለጉዳዩ በቀጠሮው ሲቀርብ ጉዳዩ መታየት ሲጀምር የእከሌ ተቃዋሚ ፓርቲ አባል ነኝ ሲል፤ እሺ ይሉና የፓርቲውን ደንብና ዓርማ ያወጣሉ፡፡ የፓርቲው ደንብ አንቀፅ እንደዚህ ወይንም ንዑስ አንቀፅ እንደዚህ ምን ይላል ይሉታል፡፡ አባል ከሆነ ጠንቅቆ ማወቅ እንዳለበት ያውቃሉና፡፡ ግለሰቦቹ ስለማያውቁት ምንም መልስ የለም፤ ሌላ አንቀፅ ይጠይቃሉ መልስ የለም፡፡ የፓርቲው ዓርማ ምን ዓይነት ነው መልስ የለም፡፡አውጥተው ያሳያሉ አያውቁትም፡፡ እሺ መሪዎቹ እነማናቸው መልስ የለም፡፡ በዚህ መልኩ ብዙዎቹ ተዋርደዋል፡፡

የተሻለ ኑሮ ፍለጋ ውጭ ሂደው የራሳቸውንና የቤተሰባቸውን ህይወት ለመለወጥ የሚያደርጉት ጥረት እንደሆነ እየታወቀ በተቃዋሚነት ስም መነገዱ አግባብነት የለውም፡፡ ይኼ የሀገሪቷን መልካም እድገትና ልማት ጥላሸት ለመቀባት ገጽታዋን ለማበላሸት ሲል ተቃዋሚው የሚጫወተው ቁማር ነው፡፡ ጥገኝነት ሳያገኙም ተሸሎክሉከው የሚኖሩት እልፍ ናቸው፡፡

በአቅም ሀገር ላይ ሰርቶ መኖር ሲቻል ይኼ ሁሉ መንከራተት አስፈላጊ አልነበረም፡፡ ግለሰቦቹ ቀንቷቸው ሕይወታቸው ቢለወጥ፣ ሰርተው አግኝተው ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን ቢረዱ እሰዬው ነው፡፡ ማንሳት የተፈለገው ተቃዋሚው በዚህ መልኩ ምን ያህል በዜጎች ሲነግድ እንደኖረ ለማሳየት ነው፡፡

የተቃዋሚውን ፖለቲካዊ ቁማር የሚያሳየው ሌላው ነጥብ ለተሻለ ኑሮና ሕይወት ሥራ ፍለጋ የተሰደዱ የኢኮኖሚ ስደተኞችን በመንግሥት ጫና እንደተሰደዱ የፖለቲካ ስደተኞች አድርጎ ሲነግድበት መክረሙ ነው፡፡

ከብዙ በጥቂቱ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች ይህን በመሰለ የዜጎችን ገንዘብ በመመዝበር ንግድ ጭምር ለበርካታ ዓመታት እስከ ዛሬም ተሰማርተው የኖሩ ከዚህ ንግድም ሆነ ከሌላ በሚገኘውም ገንዘብ እርስ በእርስ ሲባሉ፣ ሲናጩ፣ ሲወነጃጀሉ የመኖራቸው እውነት ነው፡፡

ለሕዝብ አሳቢዎች ተቆርቋሪዎች ነን፣ ሀገሬ እናቴ ባንዲራዬ እያሉ የሚያላዝኑት ሕዝቡንም ሆድ ማስባስ የሚፈልጉ ማፍያዎች እነዚህ ናቸው፡፡

በቅርቡ አዲስ አበባ ውስጥ በምስጢር ከተቃዋሚው እና ከሲቪል ሶሳይቲው ተወካዮች ጋር በምርጫ 2007ቱ ላይ የመከረው የአውሮፓ ለጋሾች (የምዕራባውያን መንግሥታተት) ቡድን በሀገር ውስጥም በውጭም ባሉት ተቃዋሚዎች ላይ ሙሉ በሙሉ ተስፋ መቁረጡን በማያሻማ ቋንቋ ነግሯቸዋል፡፡

የፖለቲካ ምህዳር ጠበል በማለት መንግሥትን የምትከሱት ዋነኛው የፖለቲካ ምህዳሩን ያጠበባችሁት እናንተም ጭምር ተጠያቂ ናችሁ፡፡ የሰለጠነ የፖለቲካ ባህልና በልዩነት ተቻችሎ ለሀገር የመሥራት ፍላጎት የጠራ ሀገራዊ አጀንዳና ግብ የላችሁም፡፡አንድ ዓይነት ዓላማ ይዛችሁ ብዙ ቦታ የምትከፋፈሉ ስሜታዊና በግለሰብ ንግግር የምትመሩ ናችሁ፡፡

አሉባልታና ያልተጨበጠ ወሬ የምታወሩ በተግባር ውስጥ የሌላችሁ ናችሁ፡፡ በሀገር ውስጥም በውጭም ላለው ተቃዋሚ ከእንግዲህ ምንም ዓይነት ድጋፍና እርዳታ አናደርግም፡፡ ምክንያቱም የሀገራችንን ብሔራዊ ጥቅም የሚነካ ጉዳይ ነው ሲሉ ገልፀውላቸዋል፡፡

ይህ የአውሮፓውያኑ የመደምደሚያ ሀሳብ የበርካታ ዓመታት ጥናትና ክትትል ውጤት ነው፡፡ የውስጡም የውጪውም ተቃዋሚ በጥላቻና በስሜታዊነት በወሬና በአሉባልታ ተወጥሮ ሲጎፈላ፣ ሲያናፍል፣ ሲደነፋ የሚውል በዓይን የሚታየውን ግዙፍ ሀገራዊ እድገትና ልማት ጌቶቻቸው ምዕራባውያኑ መንግሥታት አለም ባንክ

አይ.ኤም.ኤፍ በአድናቆት የተቀበሉትን ሽምጥጥ አድርጎ የሚክድ በጎውን በጎ ለማለት ያልተፈጠረ በመሆኑ ለሀገርም ለህዝብም እንደማይበጅ አውሮፓውያኑ ጠንቅቀው አውቀውታል፡፡

ምዕራባውያኑ የኢትዮጵያን ተቃዋሚ ኃይሎች (ፓርቲዎች) በራሳቸው ፍቅር የተነደፉ እብሪተኛ አምባገነን ዳተኛ እኔ ያልኩት ካልሆነ ባይ ሌላውን በልዩነት የማያከብሩ የሀሳብ ልዩነትን የማይቀበሉና የማያስተናግዱ የሰለጠነ የፖለቲካ እውቀትና ባህል እንደሌላቸው ለዓመታት አጥንተዋቸዋል፡፡

የኢትዮጵያ ተቃዋሚ በከረረና በመረረ ጥላቻ የተዘፈቀ በመሆኑ የሀገሩን ብሄራዊ ጥቅምና የህዝቡን ሠላም በሚያናጋ መልኩ ከማን ጋር እንደተሰለፈ የሚያውቁት ምዕራባውያኑ ከአልሸባብ ጋር ለመሥራት መቆሙን የእነሱንም ብሄራዊ ጥቅም የሚነካ በመሆኑ በቀላሉ ሊያልፉት አይችሉም፡፡

በእጅ አዙር እነሱንም እየወጋ ነውና፤ ለዚህ ነው የሀገሩንና የሕዝቡን ብሄራዊ ጥቅም መለየት ያልቻለ የጠራ ሀገራዊ መስመርና ግብ የሌለው ሲሉ በብርቱ የነቀፉት፤ ለዚህ ነው በአንዲት ከድህነት ወደ እድገት ከጨለማ ወደ ብርሀን ለመውጣት ታላቅ ተጋድሎ በምታደርግ ሀገር ላይ ስመ ብዙ አርባና ሀምሣ ተቃዋሚ ፓርቲዎች መፈልፈል ፋይዳ የማይኖረው፡፡ ሁሉም ማለት በሚቻል መልኩ ሀገራዊ የፖለቲካ እውቀትና ግንዛቤ መናጢ ድሆች ናቸው፡፡

የፖለቲካ አስተሳሰብን በልዩነት ይዘው ተቻችለው ተከባብረው ተደማምጠው ለጋራ ሀገራቸው መቼም የሚሰሩ አይደሉም፡፡ በንቀትና በመነሻሸም በአሉባልታ የተጠመዱና የተሰለፉ ሀገራዊ ታላቅ የእድገት ራዕይን ሊያሳኩ የማይችሉ፤ ብሄራዊ ራዕይም የሌላቸው፤ ለሕዝቡም ለሀገሪቱም የማይጠቅሙ ናቸው፡፡

ምክንያቱም በጎጥና በዘረኝነት ልክፍትየሚናውዙ፣ ለበቀል ያሰገጉ፣ ህዝብን አስማምተውና አቻችለው በሠላም ለመምራትና ለማስተዳደር የማይችሉ በመሆናቸው ነው፡፡

ይልቁንም ለትውልድም የመከባበርና የመደማመጥ በጋራ ለሀገር መቆምና መሥራትን የሚያስተምሩ ሳይሆኑ ጥላቻ እየዘሩ እንዲጠፋፉ የሚመክሩ የአሳፋሪና የመጥፎ ተግባር ተምሣሌቶች ናቸው፡፡

ሕዝብና መንግሥት እጅና ጓንት ሆነው ለሀገር እድገት ሠላም እየሰሩ ታላቅ ለውጥ አስመዝግበዋል፡፡ ለበለጠ ለውጥም ይሰራሉ፡፡ የሀገር ውስጡንም ሆነ የውጭ አክራሪ የዳያስፖራ ተቃዋሚውን ጉዳይ  በተመለከተ ግን ህዝቡ በቃችሁን ብሏቸዋል፡፡ ከእነሱ የሚጠብቀው ምንም ነገር የለም፤ አርፋችሁ ተቀመጡ ሥራዬን ልስራበት እያለ ነው፡፡

ጆሮ ካላቸው ያዳምጡ፤ ከጥላቻና ከበቀል ስሜት ይውጡ፤ በጎ በጎውን ያስቡ፤ ካላዳመጡ ከስህተታቸው ካልተማሩ በሀገር መቀለድ አይቻልምና ህዝቡ የግድ እንዲያዳምጡ ያደርጋቸዋል፡፡